# *ደብዛቸው ለጠፉ ታጋዮች በዊንፔግ ካናዳ የተደረገ ሕዝባዊ ምሽት*

## *The night of the Disappeared in Winnepeg , Canada*

እስካሁን ብቻ ከ$280 ሚሊዮን ብር ውጭ ሆኖ የተመሰረው የካናዳ ሰብአዊ መብት ሙዚየም ለሕዝብ ክፍት ከተደረገ በኋላ በዊንፔግ ከናዳ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ከሌሎች በአካባቢው ከሚገኙ ለሰው ልጅ መብት መከበር፣ እኩልነትና ነፃነት ከሚታገሉ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ያዘጋጁት በዓለም ውስጥ ከተለያዩ አገሮች ለሰው እኩልነት፣ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር ፣ ለፍትሕና ለነፃነት ስታገሉ ድብዛቸው የጠፉ ታጋዮችን የሚያስታውስና ለወደፊቱ እንደዚህ ዓይነት ድርጊት እንዳይፈጸም ምን መደረግ እንዳለበት የሚያሳስብ ሕዝባዊ ምሽት ቅዳሜ ጥቅምት 15 ቀን 2007 ዓ.ም (Saturday, October 25, 2014) የካናዳ ኢሚግሬሽን ሚኒስቴር፣ የዊንፔግ ከተማ ገዢ ለመሆን ውድድር ላይ የሚገኙት ግለሰብ፣ በዊንፔግ ከተማ የሚገኛው ቅድስተ ማርያም የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አስተዳደሪ አባት አባ ፍቅረስላሴ፣ ከተለያዩ ድርጅቶች ተወካዮች ፣ ከሰሜን አሜሪካው የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስራኞች አንድነት ኮሚቴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሁለት አባላት ፣ ጋዜጣኞች፣ በዊንፔግ አካባቢ የመጡ ኢትዮጵያዉያንና የሌላ አገር ዜጎች በተገኙበት በwest End Cultural Centre, Winnipeg, Manitoba, Canada ሕዝባዊ ምሽት ተደርጓል።

ፕሮግራሙ የተጀመረው በ6:30ፕም በሴንቴራል የጊዜ አቆጣጠር ነው።ምሽቱ የተካሄደበት ስብሰባ አደራሽ በሙሉ ምድርና ፎቅ በሰው ተሞልቷል። አደራሹ በትልቅ በውዱ የአገራችን ሰንደቅዓላማ በአረንጓዴ -ብጫ- ቀይ ተውቧል። መድረኩ ላይ ከትልቁ እስክርን በስተቀኝ በኩል በአማርኛና በእንግሊዝኛ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ( SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)) የሚል ፖስተር በትልቁ ተጽፏል። የምሽቱ ዋና አጀንዳ ከስር በትልቁ ***' Where are the disappeared?'*** በሚል ጽሑፍ ለሁሉም ተሰብሳቢ ግልጽ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ በፖስተሩ ላይ ተጽፎ ይታያል። ከታች ዝቅ ብሎ በፖስተሩ ላይ በወያኔ የተገደሉና ደብዛቸው የጠፉ የኢሕአፓ ታጋይ መሪዎችና አባላት የነበሩት የጸጋዬ ገበረመድህን ( ደብተራው) ፣ ጋይም ገብረእግዜብሔር፣ ተስፉየ ታደሰ፣ አበራሽ በርታ፣ ለማ ጋይሉ ፍቶግራፋቸውና ስማቸው በፖስተሩ ላይ ተለጥፏል። እንደዚሁም የሌሎች በወያኔ የተገደሉና ድብዛቸው የጠፉት ይስሐቅ ደብረጽዮን፣ በለጠ አመሃ፣ ሐጎስ በዛብሕ ፣ ተክሌ ገብረስላሴ ፣ ስጦታው ሁሴን፣ ደሳለኝ አምሳሉ፣ አዛናው ደምሌ( ቱሉ) ፣ዮሴፍ አየለ ባቲ፣ ደረጀ ቀናዓ፣ ሼክ አሊዩ አሕመድ ፣ ካሳሁን ከበደ፣ አናኖ ሚቲ ፣ በኪሳ ሲና፣ ኢዮብ ተቀበ፣ ደምሴ ተስፋዬ ፣አባይነህ ሽፈራው ፣ድሉ ገበየሁ፣ ጌታቸው ወርቅነህ፣ ጌታቸው --፣ አበበ አይነኩሉና ሌሎችም በሚል ዝርዝር በእንግሊዝኛ በፖስተሩ ላይ ተጽፎ ይነባባል። ክፍሉ ሞልቶ ንግግር እንዲያደርጉ የተገበዙ እንግዶች ቦታቸውን እንደያዙ የካናዳ የኢምግሬሽንና ሰራተኛ ሚኒስቴር ፣ቀደም ብለው የኦታዋ የፓርላማ ተወካይ የነበሩት ዘንድሮ የዊንፔግ ከተማ ሹም (Mayer) ለመሆን የሚወዳደሩት ወ/ሮ ና ሌሎች እንግዶች ወደ ፖስተሩ እየመጡ በፖስተሩ ላይ ከተለጠፉ ፎቶግራፎችና የስም ዝርዝር ጋር ፎቶግራፍ መነሰት ጀመሩ። ከሶሴፕ ሊቀመንበርና በዝግጅቱ ከፍተኛውን የማስተባበር ሚናቸውን ይወጡ ከነበሩት ከአቶ አሊ ሁሴን ጋር በመሆንም ደብዛቸው ከጠፉ ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ፎቶግራፎችና ስም ዝርዝር ጋር የማስታወሻ ፎቶ ሲነሱ ነበረ።

ምሳሌ አሊ ወደ መድረኩ ወጣ ብላ እንግዶችን እንኳን ደሕና መጣችሁ ካላች በኋላ እራት እንዲበሉ ጋበዘች። የአሊ ቤተሰቦች በሙሉ በወ/ሮ አይኔ እየተመሩ ሌሎችንም በማስተባበር እራቱን የማስተናገድ ሥራ በሥነሥርዓት ሲወጡ ተመለከትን። ተሰብሳቢዎቹ እራት ከበሉ በኋላ ብዙ እንቅስቃሴዎች በመድረኩ ላይ ተካናወኑ። ትልቁ እስክርን ሥራውን ጀመረ። ደብዛቸው የጠፉ ግለሰቦችን ዝርዝር ፣የታሰሩበት ዓመተ ምሕረት ፣ ከእስር መፈታትና አለመፈታት ፣ የታሰሩበትን ምክንያት ፣ የአንዳንድ ታሳሪዎችን እድሜ፣ የታሳሪዎችን ዓይነት በሙያ፣ የታሰሩበትን አገር ስም የሚያሳይ መረጃ እስክርኑ በመደጋገም አሳየ። እስክርኑ ሥራውን ዝግጅቱ እስካባቀበት 9:33 ፕም ድረስ በማሳየት ቆየ።የታሳሪዎቹ ትንሹ እድሜ 15 ዓመት፣ አንድ ሰው ብቻ ከእስር እንደተፈታ በአስክርኑ ይታይ ነበር። እንዲሁም አንድ ፖሊስ ተኩሶ የገደለበት ግለሰብ ስም ታይቷል። የታሳሪዎቹ ዓይነት ከገበሬ ጀምሮ እስከ ዶ/ር ድረስ ሆኖ የእድሜና የስራ ልዩነት ሳይገድባቸው ሁሉም የቆሙት ለሰው ልጅ እኩልነት፣ መብት መከበር ፣ ነፃነትና ፍትሕ ነው። በእስክርኑ ላይ ይታይ ከነበረው ጽሑፍ መረዳት የቻልኩት ደብዛቸው የጠፉት ሰዎች ብዙዎቹ የሰብአዊ መብት ተሞጋቾች፣ በግጥም ለሰው መብት ተከራካሪዎች( ገጣሚዎች)፣ ለሰራተኞች መብት ተከራካሪ የሆኑ የሰራተኛ ማህበራት መሪዎች፣ ለማሕበረሰብ መብት የቆሙ መሪዎች፣የተለያዩ አገር

መሪዎች በሕዝብ ላይ የሚፈጽሙትን ወንጀልና በደል የሚቃወሙ የሕሊና እስረኛች፣ የሴቶች መብት ተከራካሪዎችና በአጠቃላይ ለሰው ልጅ መብት እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ግለሰቦች( Activists) መሆናቸውን ነው። መደረግ ያለበትን ቅዱስ ተግባር የፈጸሙ የዓላማችን ፋና ወጊዎች የነበሩ ናቸው ። እነዚያን ለሰው ልጅ መብት የቆሙትን ግለሰቦች ደብዛ ያጠፉ አገሮችም ስም ዝርዝር በእስክርኑ ላይ ይታዩ ነበር። የሚከተሉት ናቸው፡- ኢትዮጵያ ፣ ቬትናም፣ እንዶኔዢያ፣ ካምቦዲያ፣ ሕንድ፣ራሺያ፣ ቺቺኒያ፣ ኮሎምቢያ፣ ሶሪያ፣ፊሊፒንስ፣ ኤርትራ፣ ጋምቢያ፣ ቻይና፣ ኤልሳልቫዶር፣ የኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ፣ ካሜሮን፣ ቺሌ፣ የዶሚኒካን ሪፑብሊክ፣ ቡሩንዲ፣ ሚክሲኮ፣ጎትማላ፣ ካናዳ( ዊንፔግና ሰሜን ማንቶባ)፣ ቱኒዚያ፣ ናይጀሪያ፣ አልጄሪያ፣ዩክሬን፣ አሜሪካ፣ፓክስታን፣ ማሌዢያና ማውርታኒያ ናቸው። በጠቅላላ 30 አገሮች። የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኛች አንድነት ኮሚቴ ግንኙነት በማድረግ በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገውንና አሁንም እየተደረገ ያለውን ሰብአዊ መብት ረገጣና ሌሎች ወንጀሎችን ለማሳወቅ አብሮ በመስራት ላይ የሚገኘው ከላይ ከተዘረዘሩት አገሮች ከተወጣጡ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር ነው። ይህ ራሱ ትልቅ ክንውን ነው። ለዚህ ሶሴፐና የድርጅቱ ሊቀመንበር አቶ አሊ ሁሴን ምስጋና ይገባቸዋል።

ከዚያም ዋናው ፕሮግራም በዊኒፔግ የሰው መብት በኢትዮጵያ እንዲከበር እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ (Ethiopian Youth Human Rights Activist) በምትገኘው በወጣት ምሳሌ አሊ መሪነትና የመክፈቻ ንግግር ተጀመረ። ወጣት ምሳሌም በስብሰባው መገኘት የሚገባቸው እንግዶች በአደራሹ እንደተገኙ በማሳሳብ ስብሰባውን መቀጠል እንደሚቻል ገለጸች። በዓለም በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ቦታዎች ለሰው ልጅ መብት ፣ ነፃነት፣ እኩልነትና ፍትሕ የቆሙ ወገኖች ደብዛቸው እየጠፉ መሆናቸውን ፣ ቁጥራቸውም እየጨመረ እንደሆነ ፣ቀደም ብለው በጨካኝ መሪዎች ደብዛቸው የጠፉት አሁንም ያሉበት ቦታ እንደማይታወቅ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በቅርቡ ለ23 ዓመታት ደብዛቸው ጠፍቶ የቆዩት የኢሕአፓ አመራርና ነባር አባላት የነበሩት ጸጋዬ ገብረመድህን( ደብተራው )፣ ይስሐቅ ደብረጽዮን ፣ በለጠ አመሃ ፣ ስጦታው ሁሴን ፣ ሐጎስ በዛብህ ፣ ደሳለኝ አምሳሉ ፣ ተክላይ ኃይለሥላሤ ፣ አዛናው ደምሌ በአንድ የወያኔ ባለስልጣን በነበረው ግለሰብ አማካይነት ያለፍርድ ቤት ውሳኔ የተገደሉ መሆናቸው መገለጹን ስም ዝርዝራቸውን እያነበበች ገለጸች። ቤቱ በዝምታ ተዋጠ። ከዚያም ቀጥላ በምሽቱ ንግግር እንዲያደርጉ ተጋብዘው የነበሩት አባ ፍቅረሥላሤ ጸጋው በማንቶባ ጠቅላይ ግዛት በዊንፔግ ከተማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የቅድስተ ማርያም ቤተክርሲቲያን ኃላፊ ንግግር እንዲያደርጉ ጠየቀች። አባ ፍቅረሥላሴም ለሰው ልጆች መብትና እኩልነት ሲታገሉ ደብዛቸው የጠፉ ሰዎችን ለማስታወስና ሕዝብ እንዲያውቅ ይህንን ስብሰባ ያዘጋጁትን በሙሉ አመስግነው በተለይ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴና የኮሚቴው ሊቀመንበር አቶ አሊ ሁሴን ያደረጉትን አስተዋጽዖ ትልቅ ተግባር ነው ብለዋል። ለሰው ልጅ መብት፣ እኩልነት ፣ ነፃነትና ፍትሕ መቆም በዘር፣ በሃይማኖት ፣ በፖለቲካ ልዩነት የማይደረግበት አስፈላጊ ሥራ ነው። ለዚህ ዓይነቱ ተግባር ሁላችንም መተባበር ያስፈልጋል። በስብሰባው የተገኙትንም አመስግነዋል። የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በተለያዩ ዓለማት በኢትዮጵያ፣ በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ ታሰረው የሚገኙ ኢትዮጵያዉያንን ወደ ታሰሩበት ቦታ በመሄድ መጠየቁ፣ የዓለም ሕዝብ በወገኖቻችን ላይ የሚፈጸመውን በደል እንዲያውቁ ማድረጉ ትልቅ ስራ ስለሆነ እኛ ኢትዮጵያውያን ይህንን ድርጅት መተባበርና ማገዝ ያስፈልጋል። በ2015 የሚደረገውን የጠፉ ዜጎችን ለማስታወስ የሚደረገው ምሽት የተሳካ እንዲሆን ሁላችንም የበኩላችንን ድርሻ መወጣት ይኖርብናል ፤ በተለይ ኢትዮጵውያን በበለጠ መንቀሳቀስ ያስፈልጋናል፤ እኔም በማስተባበር ታሳትፎ አደርጋለሁ ብለዋል። እኔና ሌላ አንድ ግለሰብ ስብሰባው ሲያልቅ አባ ከአደራሹ ሲወጡ ጠብቀን የመጠነው ከሌላ ቦታ ነው ለሚቀጥለው ዓመት በሚደረገው ስብሰባ ላይ ለመገኘት የእርስዎን የዛሬውን ጥሪ ተቀብለናል በማለት ገልጸናል። ላዳረጉትም አርአያነት ላለው ለአገርና ሕዝብ የሚጠቅም ተግባር ከሌሎች ግለሰቦችም ምስጋና ስቀርብላቸው ለማየት ችለናል።

ከዚያ ቀጥሎ የተካሔደው በአደራሹ ለሚገኙ ተሰብሳቢዎች በሙሉ ተሰጥቶ የነበረው ሻማ አደራሹ ጨለማ ሆኖ እንዲቀጣጠል ማድረግ ነበር። በጨለማ ውስጥ ጭልጭል የሚል ብርሃን ፈነጠቀ። ምሳሌውም በሕዝብ ላይ በየአገሩ የሚገኙ ጨካኝ መሪዎች የሚያደርሱትን በደል ጥቂቶች እራሳቸውን እየሰዉ ለሰው ልጅ መብት ፣ እኩልነት፣ ነፃነት ፣ ፍትሕ የሚያደርጉትን መስዋዕትነት ማብሰር ነው። ሕዝብ ለዘለዓለም የአምባገነኖች መጠቀሚያ ሆኖ እንደማይኖር በትግልና በመሰዋዕትነት መብቱን ማስከበሩ የማይቀር መሆኑን ማሳያ ነበረ። በተለያዩ አገሮች ድብዛቸው የጠፉት ታጋዮች ለሰው ልጅ ማህበራዊ እኩልነት እንደሻማ እየቀለጡ ለነፃነት ለሚደረገው ትግል የሚኖራቸው ሚና ቀላል እንዳልሆነ የሚያሳይ ሥራ ነው በሻማው መቅለጥና በጨለማ ውስጥ በሚበራው ብርሃን ለማስተላለፍ የተደረገው ምሳሌያዊ ተግባርም የሚደነቅ ነበር።

የድጋፍ መልእክቶች ከሚከተሉት ድርጅቶች በምሽቱ ለሕዝብ ቀርቧል። እነሱም፡-

- Canadian Immigration& Labor Minister
- የቅድስተ ሥላሴ ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርሲቲያን በዊኒፔግ ማኒቶባ ( Trinity St. Mary's Ethiopian Orthodox Church in Winnipeg, Manitoba)
- Aborijinal Representative in Winnipeg
- Winnipeg Multicultural human rights forum
- Chilean human Rights Council
- Winnipeg Social Planning Council
- Human Rights Song Singer
- ሰሜን አሜሪካ ቅርንጫፍ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ( Solidarity Committee for Ethiopian Political Prisoners in North America Chapter)
- African Cultural Performance
- Winnipeg Amnesty International Representative
- Winnipeg Peace makers Representative

ሁሉም ተነጋሪዎች ለሰው ልጅ መብት፣ እኩልነት ፣ ነፃነትና ፍትህ የሚደረገውን እንቅስቃሴ በመደገፍ ንግግርና ሙዚቃ ያቀረቡ ሲሆን ሁሉም በተለያዩ አገሮች ለሰው ልጅ መብት በመቆማቸው ደብዛቸው ጠፍቶ የሚገኙ ታጋዮችን በየዓመቱ ማስታወስ ፣ ይህንን ተግባር ለመፈጸም የተመሰረቱ ድርጅቶችን መርዳትና ቤተሰቦቻቸውን መጠየቅ እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። በሰው ልጅ የሚደረገውን የዘር መድልዎ በተመለከተ የአቦርጂናሎችም ጉዳይም ተነስቶ ነበር። አቦርጂናሎች በተለያዩ አገሮች በአሜሪካ፣ በአውስትራሊያ፣ በጀርመን፣ በካናዳና በሌሎች አገሮች የሚገኙ የየአገሮቹ ቀደሚ ሕዝቦችና ኖሪዎች ናቸው። ይህ የሕዝብ ክፍል አገራቸውን የወረሩ ኮሎኒያሊሶች( ቅኝ ገዢዎች) ግፍ ፈጽመው ከሌላ መጤ ሕዝብ እንዳይገናኙ በማድረግ በአዳሪ ት/ቤት፣ ለእነሱ ብቻ በተከለሉ ቤትክርሲቲያኖችና ቦታዎች እንዲቀመጡ ተደርገው በትምህርት፣ በጤና ፣ በኢኮኖሚና በፖለቲካ ከፍተኛ በደልና ጥቃት ሲፈጸምባቸው የቆዩና አሁንም በአንዳንድ አገሮች ውስጥ በችግር ላይ የሚገኙ ናቸው። በካናዳ በ2011 በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ መስረት ከአገሪቱ አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት 4.3% አቦርጂናሎች ናቸው። ለእነዚህ ሕዝቦች በመንግሥት በኩል አንዳንድ የኑሮ ሁኔታዎችን ለመሻሻል ጥረት ቢዳረግም አሁንም በተወሰነ ደረጃ በሕዝብ በኩል የመገለልና ሌሎች ችግሮች ላይ የወደቁ ናቸው። በካናዳ የሚገኙ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ፣ የኢምግሬሽንና የሙያ ሚኒስትር መ/ቤት በእነዚህ የህዝብ ክፍል ላይ የሚደርሰውን በደል ለማስወገድ አንዳንድ ሥራዎችን እየሰሩ ናቸው። ሊያ ጋዛር የተባሉት የዊኒፔግ የማሕበራዊ እቅድ ተወካይ ስለተገደሉና ደብዛቸው ሰለጠፉ ሴቶች ጉዳይ አንስተው ንግግር አድርገዋል። አንድ ሙዚቀኛም በምሽቱ ሁለት ደብዛቸው የጠፉ ግለሰቦችን ስም በማንሰትና ደብዛቸው የጠፋበትን ምክንያት በመንገር ለእነሱ ያዘጋጀውን ሙዚቃ ለተሰብሳቢዎች አቅርቧል። ካናዳ ውስጥ ከላይ በምሽቱ እንዲሳተፉ ከተጋበዙት ድርጅቶች እንደሚታየው ብዙዎቹ ለሰብአዊ መብት የሚሰሩ ናቸው። የሰብአዊ መብት ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት ያለበት የሕዝብ አጀንዳ ነው። ኢትዮጵያውያን ለዚህ ጉዳይ ከተንሻዋረረ አመለከት ጸድተን ብዙ መሥራት ይጠብቅናል።

የሰሜን አሜሪካ ቅርንጫፍ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴን ወከለው የምሽቱ ዋና ተነጋሪ የነበሩት አቶ ጌድዮን አዳዳ በምሽቱ የነበሩ ተሰብሳቢዎችን ልብ የነካ ንግግር አድርገዋል።የተወሰነው እነሆ፡- ከዓለም ውስጥ አምባገነን መሪዎችን ለማስወገድና ደብዛቸው የጠፉ ታጋዮችን ለማስፈታት ትግል ማድረግ ፣ ደብዛቸው ጠፍቶ ያሉትን ታጋዮች በየዓመቱ ማሰቡና ይዘው የተነሱበትን ዓላማ አንግቦ መራመዱ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አሳስበዋል።ይህንን በማድረግ ከዓለም የአምባገነኖችን ሥርዓት ተወግዶ ሕዝብ ወሳኝ የሚሆንበት እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በመፍጠር በዓለም ውስጥ ለሰው ልጅ መብት የሚቆሙ ታጋዮችን የመሰወሩ አስነዋሪ ተግባር መጥፎ የታሪክ አሻራ ሆኖ እንዲቀርና ደግም እንዳይኖር ማድረግ ያስፈልጋል በማለት አሳስበው፤ አያይዘውም በኢትዮጵያ በደርግና በወያኔ አምባገነን ሥርዓቶች በብዙ ሺ የሚገመቱ ኢትዮጵያዉያን እንደሞቱ ፣ እንደተሳቃዩ፣ እንደተሳደዱና ደብዛቸው እንደጠፉ ገልጸዋል። እሳቸው ገና ልጅና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ በነበሩበት ወቅት በፈረንጆች በ1970ቹ ዓመታት በሶስተኛ ወንጀል ምርመራ ክፍል

የተፈጸሙትን ሁለት ጉዳዮች ለተሰብሳቢዎች አቀረቡ። አንዱ ሰለሞን በሚል ስም ይጠረ የነበረው የኢሕአፓ አባል እስረኛ ጉዳይ ነበረ።ሰለሞን የደርግ መርመሪዎች እንደሚገሉት በመረዳቱ የሚወዳቸው እናቱ የኔን መሞት( መገደል) ሳታውቅ አልሞትም ይል ነበር። ሰለሞን እንደተነገረው የደርግ ነፍሰገዳዮች ሊገድሉት ከእስር ቤት ስሙን ጠርተው አወጡ። የተወሰነ እርምጃ በመኪና ይዘው ከተንቀሳቀሱ በኋላ ለነፍሰገዳዮቹ በእናቱ አልጋ ስር ታንክ እንደደበቀና ለማሳየት እንደሚፈልግ ይነግራቸዋል። ሰውን ለመደብደብና አካላትን ለመስበር የተካኑት ደንቆሮ የደርግ መርመሪዎች ታንክን ያክል ትልቅ የጦር መሳሪያ ከቤት ውስጥ ለመግኘት ሰለሞንን ይዘው ወደ እናቱ ቤት ገሰገሱ። በውድቅት ሌሊት ቤታቸውን አስከፍተው የሰለሞንን እናት ታንኩን ከአልጋ ስር እንዲያወጡ ይጠይቃሉ። ሰለሞን በመሀል ገብቶ ምንም መሳሪያ የለም። ለእናቱ መገደሌን እንዲታውቂ ፈልጌ ነው እነዚህን ሰዎች ይዤ እዚህ የመጣሁት ይላል። ከዚያም ነፍሰገዳዮቹ ተነደው ሰለሞንን በእናቱ በራፍ ላይ እንደገደሉ ገለጸ። ሁለተኛው በሶስተኛ ወንጀል ምርመራ ወቅት የሚሞቱ ሰዎች ትተውት የሚሄዱት አንድ እቃ ቢኖር ጫማ ብቻ ነበር። በእስሩ ቤት ውስጥ የጫማ ክምር ብዙ ነበር። ሞቾቹ ጫማቸውን የሚታውቡት ምክንያት እግራቸው በስየል ስለአበጠና ሰለመረቀዛ ጫማ ማድረግ ያስቸግራቸው ስለነበረ ነው። ***“ዛሬ እነሱ ሞተዋል። የሉም። የእነሱን ጫማ ተጨምተን በመሔድ ትግሉን መቀጠል ያለብን እኛ ነን። ”*** በዓለም ውስጥ አምባገነኖች ባሉበት ቦታ ሁሉ የሚፈጸመው በደል ሊቆም የሚችለው ሁላችንም ደብዛቸው የጠፉ ታጋዮች ይዘውት የተነሱትን ሕዝባዊ ጥያቄዎች በመንገብ መታገል ስንችል ብቻ ነው። ይህን እናድርግ በማለት አሳሰቡ። ንግግራቸውንም በዚህ ቆጩ። በአድራሹ የነበረው ሕዝብ በሙሉ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ድጋፉን በጭብጨባ ገልጿል።

በመጨራሻም በየትኛውም ቦታ የተወሰኑ ግለሰቦች በበጎ መልኩ የሚያደርጉት አስተዋጽዖ ብዙ ሰዎችን ሲጠቅም በታሪካችን አይተናል። ከዚህ አንጻር አቶ አሊና ቤተሰቦቹ የሚያደርጉት ሥራ ትልቅ ትምህርት ለሁላችንም የሚሰጥ ነው። ቤተሰቦቻችንን እናደራጅ። ለአገራችውና ለሕዝባቸው የሚኖራቸውን ኢትዮጵያዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ እናድርግ። ዝግጅቱ በዓለም ዙሪያ ለሰው ልጅ መብት፣እኩልነት፣ ነጻነትና ፍትህ የሚደረገው ትግል ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን፣ በዓለም ውስጥ ሕዝብ የሚበድሉ አምባገነኖች የበረከቱ መሆናቸውን፣ በዚያው ልክ የሕዝብ ጸር የሆኑትን መሪዎች በማስውገድ ዲሞክራሲ፣ እኩልነት፣ ነፃነት፣ ፍትህና የሕግ የበላይነት ያለበት ሥርዓት ለመፍጠር የሚታገለው የሕብረተሰብ ክፍልም ብዙ እንደሆነ ለማወቅ ችለናል ። የስብአዊ መብት ድርጅቶችም ቁጥር እየጨመረ መሆኑን ማየት ተችሏል። በዓለም ትልቁ የሰብአዊ መብት ሙዚዬም በካናዳ ዊንፔግ ተመስርቷል። በተለያዩ የዓለም ክፍል ተደብቀው የሚገኙትን ( ለምሳሌ መንግሥቱ ኃይለማርያምን ያስታውሷል) አምባገነኖችን ለአዲሱ ትውልድ ማሳወቅ የሚቻልበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። በዓለም ላይ ያሉትን የሕዝብ ጠላት የሆኑ መሪዎችን ለማስወድም በጋራ መስረት እንደሚያስፈልግ ከምሸቱ ትምህርት መቅሰም ተችሏል። በስብሰባው የንበሩት ግለሰቦች መቀራረብ ፣ ከፊታቸው ይታይ የነበረው ቁጭት፣ በጋራ በአምባገነን መሪዎች ሊዳረግ የሚገባውን ትግል በማንሰት ይዳረጉ የነበሩት ውይይቶች ለታጋዩ ወገን ብርታት የሚሰጡ ናቸው። የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴን በሁሉም መልክ በገንዘብ፣ አባል በመሆን፣ በሐሳብና መራጃ በመስጠት መጠናከሩ ኮሚቴው አሁን እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ አስፍቶና አድጎ ብዙ ሥራዎችን ለማካሄድ ይረዳል። በዚህ በኩል ኢትዮጵያውያን ይህንን እውነተኛ የሰብአዊ መብት ድርጅት ልንረዳውና ልንከባከበው ይገባናል። ድርጅቱ በተግባሩ በውስን አቅሙ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚያደርገው የተወሰኑ ጥረቶች አልፎ በዓለም ለሰው መብት ከቆሙ ድርጅቶች ጋር በመሆን ለሐቅ መቆሙን አረጋግጧል።

የጊዜ እጥረት ቢኖርም በካናዳ ዊንፔግ ከተማ የሚገኘውን በኢትዮጵያ አንድ ትውልድን የመተረው የቀይ ሽብር ታሪክ አካል የሆነበትን የካናዳ የስብአዊ መብት ሙዚየም( Canadian Human Right Museum) ለመጎብኘት ሄደን ነበር። ብዙ ሥራዎች ገና እየተሰሩ ስለሆነ እስከ ሕዳር 12 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ ሙዚየሙ ክፍት እንደማይሆን የሙዚየሙ ሰራተኞች ስለገለጹልን ሳናይ ተመለስን። መታየት ያለበት ትልቅ ሙዚዬም ነው። በመግቢያው ላይ ባሉት 10 የሙዚየሙ ዋና እርሶች ላይ የተጠቀሱትን ትምህርታዊ ጥቅሶች ፎቶ ግራፍ በማንሳትና ከአብአዊ መብት ተካራካሪ ወገናችን ከአቶ አሊ ሁሴን ጋር የማስታወሻ ፎቶግራፍ አብረን ተነስተናል። አንዳንድ ጊዜ ነጭ ሌላ ጊዜ ጥቁር በመሆን በግድግዳ ላይ የተዘጋጀ በሚመስለው ቦርድ ላይ የሰብአዊ መብት ታሪካቸው በሙዚየሙ ውስጥ የተካተቱ አገሮች ቋንቋ እንኳን ደህና መጡ የሚለው ለእኛ ለኢትዮጵያዉያን” **እንኳ ደህና መጡ”** ብሎ በአማርኛ ሲጽፉ ሰዎቹን ለማየት ስንጠጋ የሉም። ጽሁፉ ግን አለ። ነጭና ጥቁር እየሆኑ ከጠፉበት ወደዉኑ ብቅ ይሉና ስራቸውን ይጀምራሉ። የኮምፑተር የጥበብ ሥራ መሆኑ ኋላ ላይ ገብቷናል። አቶ አሊ ሁሴንን አንድ ጥያቄ ጠይቀን ነበር። የዚህ ሙዚየም ሥራ ሲጀመር ለመጀመሪያ ጊዜ ግንኙነት እንዴት ፈጠሩ ? የሚለው ነበረ። መልሳቸው የሙዚየሙ ሥራ ሲጀመር ወሬ ሰምቼ ሙዚየሙ ሥራ ወደሚካሄድበት ቦታ በመሄድ በነፃ

አገልግሎት መስጣት ቀጠልኩ ከዚያም በአገራችን ኢትዮጵያ የተፈጸመውን አንድ ትውልድን የመፍጀት ታሪክ በመንገር የሙዚየሙ አካል ለማድረግ ተቻለ ብለዋል። የሚደነቅ ተግባር ነው።

ከዚያም ሁለታችንም የአገራችንን ዘፈን እየዘፈንን፣ የEFND ክፍል ታዳሚም በመሆን ከምሽቱ 1:30 ኤም ወደ ክልላችን በሰላም ተመልሰናል። የEFND ክፍል አስተዳደሪዎችንና ሌሎች በክፍሉ የነበሩ ታዳሚዎችን ስልክ በመደወል የጠፉ ወገኖቻችን የሚታወሱበት ምሽት እንዴት እንደነበረ መረጃ እንዲንሰጣቸሁ ስለጠየቁንና ስለተባበሩን በጣም እናመሰግናለን። እንዲሁም ለዊንፔጎቹ ወገኖቻችን ለአቶ አሊ ሁሴንና ቤተሰቡ ለጌታቸውና ቤተሰቡ ለመልካም አቀባበላችሁ እናመሰግናለን። እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤ በርቱ።

ኢትዮጵያ አገራችን ለዘለዓለም ጸንታ ትኖራለች!!

ሪፖርት አቅራቢ፡ ሰውነት ፈቃዱ